# በአንዳንድ ፓርቲዎች የተቀባይነት ስጋት ምርጫው አይታገትም

ዘንድሮ በመላ አገራችን የአካባቢ ምርጫ እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች እንደራሴዎቻቸው ለተጓደሉባቸው ምክር ቤቶች የማሟያ ምርጫ እንደሚካሄድ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አስታውቋል:: በዚህም መሰረት ምርጫውን ለማስፈጸም የተለያዩ ዝግጅቶች በመከናወን ላይ ይገኛሉ::

ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ይህንኑ ምርጫ በማስመልከት በቅርቡ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በመጥራት መግለጫ መስጠቱ የሚታወስ ነው:: በወቅቱ ቦርዱ ምርጫው ሊካሄድ የሚችልበትን መነሻ የጊዜ ሰሌዳ ለፓርቲዎች በማቅረብ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ጠይቋል::

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የጊዜ ሰሌዳውን በተመለከተ ለቦርዱ በሰጠው ምላሽ ቦርዱ ባቀረበው መነሻ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ዝግጅቱን አጠናቆ ለምርጫ ለመወዳደር ዝግጁ መሆኑን የገለፀ ሲሆን ሌሎች ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ለዝግጅት ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልጉ ከሆነ ግን ምክንያታዊ የሆነ የጊዜ ጭማሪ ቢደረግ ተቃውሞ እንደሌለው ግልፅ አድርጓል::

ይሁን እንጂ ጥቅምት 16 ቀን 2000 ዓ.ም ኢዴፓህ፣ ኦፌዴን እና ቅንጅት በሰጡት የጋራ ጋዜጣዊ መግለጫ የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ በምርጫው ላይ ለመሳተፍም ሆነ ላለመሳተፍ ውሳኔ ላይ እንዳልደረሱ ገልፀዋል::

ካቀረቧቸው ምክንያቶች ውስጥ ፅህፈት ቤቶቻቸው እንደተዘጉ፣ አባሎቻቸው እንደታሰሩ፣ በቂ የመገናኛ ብዙሃን ሽፋን እንዳላገኙ፣ የፓርቲዎች ድጎማ ተግባር ላይ እንዳልዋለና የውጪ ታዛቢዎች መኖር አለባቸው የሚሉት ይገኙባቸዋል::

በመሰረቱ በአገራችን በህጋዊ መንገድ በሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችም ሆነ በአባሎቻቸው ላይ የተጣለ ምንም አይነት እገዳ እንደሌለ የታወቀ ነው:: ይህ መብት እንኳን በፓርላማ ውስጥ ለሚገኙ ፓርቲዎች ህገመንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለማፍረስ መሞከራቸው በነፃ ፍርድ ቤት ከተረጋገጠባቸውና ከተፈረደባቸው በኋላ ምህረት ጠይቀው ለወጡት ሃይሎች የተረጋገጠ መብት መሆኑም ገሃድ ሆኖ ሳለ እንዲህ አይነት ውንጀላ ማቅረብ አግባብነት የለውም::

ሚድያን በተመለከተም እስካሁን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በፓርላማ የሚሰነዝሯቸው አስተያየቶች ለህዝቡ በቀጥታ ጭምር የሚተላለፉ መሆናቸው እየታወቀና ለቀጣዩ

ምርጫ የማስታወቂያ ሚኒስቴር የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀምን በተመለከተ በምርጫ ህጉ መሰረት ከቦርዱ ጋር በመሆንና ተወዳዳሪ ፓርቲዎችን በማማከር የድልድል ሃሳብ ሳያቀርብ እንዲህ አይነት መግለጫ መስጠት ተገቢ እንዳልሆነም ግልፅ ነው::

በተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የውጪ የምርጫ ታዛቢዎችን ሊጋብዝ የሚችል ሲሆን በአካባቢ ምርጫዎች የውጪ ታዛቢዎች ተሳትፎ የተለመደ እንዳልሆነ የታወቀ ነው::

ተቃዋሚዎቹ ፓርቲዎች የፓርቲዎች የገንዘብ ድጎማ ጉዳይ በፓርቲዎች መካከል ለድርድር የቀረበ ጉዳይ መሆኑን ያውቃሉ:: ድርድሩ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ እንዳይካሄድ እንዳሻቸው ከመድረኩ እየወጡና እየገቡ ያጓተቱት ራሳቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ናቸው:: በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ላይ ከራሳቸው በስተቀር ማንም ተጠያቂ ሊሆን አይችልም::

ኢህአዴግ በትናንትናው ዕለት በሶስቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተሰጠው መግለጫ ፓርቲዎቹ ለውድድር የሚያበቃ ዝግጅት ያለማድረግ ድክመታቸውን በሌሎች ላይ ለማሳበብ ሲሉ የሰጡት መሆኑን ይገነዘባል:: ፓርቲዎቹ ባለፈው አመት በራሳቸው ጥያቄ መሰረት ምርጫው ለያዝነው አመት እንዲሸጋገር መጠየቃቸውና በዚሁ መሰረት መተላለፉ እየታወቀ ዘንድሮም የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ ከምርጫው ሂደት እግራቸውን ለመጎተት መሞከራቸው ያደረባቸውን የተቀባይነት ስጋት ከማጋለጥ ባሻገር ሌላ ፋይዳ አይኖረውም::

የአገራችን ህዝብ በመረጣቸው ተወካዮች የመተዳደር ህገመንግስታዊ መብት አንዳንድ ፓርቲዎች ባለባቸው የተቀባይነት ስጋት ምክንያት መታገት እንደሌለበት ኢህአዴግ በጥብቅ ያምናል:: ፓርቲዎቹ በምርጫው ላይ ቢሳተፉም ባይሳተፉም ህዝቡ አስተዳደሩን በምርጫ በማዋቀር የጀመረውን የልማትና የዲሞክራሲ ግንባታ ተግባሩን እንደሚቀጥል ሊታወቅ ይገባል::

በመሆኑም ፓርቲዎቹ የተለያዩ ሰበቦችን ከመፍጠርና ወቀሳ ከመሰንዘር ተቆጥበው በነርሱ ተሳትፎ ጭምር በፀደቀው በአዲሱ የምርጫ ህግ መሰረት ህግና ስርአቱን አክብረው በምርጫው ሂደት እንዲሳተፉ ኢህአዴግ ጥሪውን ያቀርባል::

**የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ)**

**ጥቅምት 17 ቀን 2000 ዓ.ም**